# ይድረስ ለጀርመን ድምፅ የዐማርኛ ቋንቋ አገልግሎት

# ቦን

በመጀመሪያ ሰላምታዬ ይድረሳችሁ።
ቀጥሎም ዛሬ ለመጻፍ ያነሳሳኝ ከሳምንት በፊት የ"አርጎብኛን ቋንቋ ከሞት ያተረፈው" ብላችሁ ስለ አርጎባ ሕዝብ ታሪክና ባሕል ያናፈሳችሁትን በሬው ላም ወለድ ትርኪምርኪ በተመለከተ መልስ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

በመጀመሪያ ደረጃ ያርጎባ ቋንቋ አልሞተም፣ ሊሞትም አይችልም። ስለምን ቢባልስ አርጎብኛ የሚባለው ቋንቋ ከዐማርኛ ጋራ ከ85% በላይ ተዛማጅ ስለሆነ የቋንቋ ሊቃውንት ያማርኛ <u>ዘዬ</u> ይሉታል። በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋ ቤተሰቦች ተመራማሪው ዕውቁ ፕሮፌሰር ወለፍ ለስላው ስለ አርጎብኛ ሰፊ የመስክ ጥናት ከ1950 ዎቹ ዓመታት ጀምሮ በአንኮበር ቆራሬ ምክትል ወረዳ አልዩ አምባና አካባቢው፤ በደቡብ ምሥራቅ ወሎ በኮምቦልቻ አካባቢ የአርጎባ ስፈሮችን እንዲሁም በሐረርጌ ክፍለ ሃገር ቢሲዲሞ የሚገኘውን የአርጎባ መንደር ቋንቋውን በማጥናት ታላቅ አስተዋፅኦ ማደርጋቸው ይታወቃል። ፕሮፌሰር ለስላው ነፍሳቸው ትማር በአልዩ አምባ ከዐማርኛ በስተቀር አንድም አርጎብኛ ተናጋሪ ሽማግሌ አለማግኘታቸውን ምን አልባትም በዱለቻና ጨኖ፣ ጋቸኔ አርጎብኛ ተናጋሪ ይኖሩ ይሆናል የሚል ዜና ብቻ የሰሙ መሆኑን መዝግበው አቆይተውናል።
ታዲያ! ሐቁ እንዲህ ሆኖ ሳላ ዛሬ በዘመነ ወያኔ ኢህሕኤዴግ በአልዩ አምባ አርጎብኛ ከማንም <u>ጋራ ሳይቀላቀል መኖሩና አዲስ</u> ተገኝቶ ከሞት አተረፈነዋል እየተባለ የሚቀባጠረው ስለምንድን ነው? በወያኔ የባንቱስታን አፓርታይድ የዘር የጎሣ ፖለቲክ መመሪያ "የአርጎባ ሕዝቦች ብሔረሰብ" የተሰኘ ተለጣፊ ከአለፈው ትክክለኛ ምርጭያ 1997 ዓ.ም ክስረት በኋላ ተዘጋጅቷል። የተለጣፊው የፖለቲክ ፓርቲም እራሱን የአርጎባ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (Argoba National Democratic Organization, ANDO) ባይ ነው። የተለጣፊው ፓርቲ ሲያሜ እስላም ዐማሮችን ለማወናበድ የተዘጋጅ መሆኑን በግልጽ ያመለክታል።

# ብሔርና ጎሣ

በኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ የተባሉት ቃላት ሰፊ ማወናበጃ ሆነዋል። ብሔር የግእዝ ቃል ትርጉሙ <u>አገር</u> ነው። አገር ስንል ደግሞ ሕዝብና መንግሥት ያለው ልዑላዊ የግዛት ወሰኑ የተዋቀ ማኅበረሰብና ባሕልን ያጠቃልላል። መንግሥትም የአንድ ማኅበረስብ ድርጅታዊ መዋቅር ነው። አገርና መንግሥት ጥንትም ሆነ ዛሬ በዘር፣ በሃይማኖትና በጎሳ መስፈርት በጭራሽ አይገለጹም። ለምሳሌ በአውሮፓ አህጉር ከሮማውያኑ ትልቅ ግዛት ማክተም ጀምሮ በየስፍራው ልዩ ልዩ አገሮች ተመሥርተዋል። የፈረንሳይ፣ የእስፓኝ፣ የፖርቱጋል፣ የጣሊያን፣ የእንግሊዝ፣ የስኮት፣ የጀርመን፣ ወዘተረፈ

ከፈረንሳይ አብዮትና የስብአዊ መብት የይስሙላ አዋጅ እወጃ ወዲህ በአውሮፓ ብሔራዊ መንግሥታት (Nation States) ይልቁንም በቅርቡ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ብዙ አገሮች ተቋቁመዋል። ኢትዮጵያ በአገርነት ከዓለም ላይ በአንጋፋነት የምትጠቀስ ናት።

በኮሚኒስታዊ ርእየት የብሔር ትርጉም ታሪካዊ ማኅበረሰብነት ያላቸው ሰዎች በአንድ የጋራ ግዛት፣ የጋራ ምጣኔ ሃብት ትስስር፣ የጋራ ሥነ ጽሑፍዊ ቋንቋ፣ እንዲሁም አጠቃላይ ባሕርይና ባሕላዊ መለያ ሲፈጥሩ ነው።

በኢትዮጵያ ምድር በኮሚኒስቶች የብሔር ትርጓሜ እይታ አንድም እንኳ ነገድ ለብቻው <u>ብሔር</u> ሊባል ከቶ አይችልም። የኢትዮጵያን ሕዝብና ማኅበርሰብ ለመከፋፋፈል ታስቦ ብቻ በቅጥረኞች ብሔር ብሔረሰብ በታባሉት ቃላት ሽፋን የነፃ አውጪ ግንባር ተብዬዎች አንዱን ነገድ ወይም ቋንቋ ተናጋሪ ብሔር፣ ሌላውን ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ ብሔረሰብ እያሉ ያወናብዳሉ። ዐማርኛ ተናጋሪውን ወገን በጠላትነት መድበው ጨቋኝ ብሔር ይሉታል። ሌሎቹ ሁሉም በጅምላ ተጨቋኝ ብሔሮች ሆነዋል።

የሚያስገርመው ደግሞ በቁጥር አናሳ የሆኑት ትግሪኛ ተናጋሪዎች ብሔር ሲሆኑ በቁጥር ላቅ ያሉት የጉራግኛ፣ የሲዳምኛ ወዘተረፈ ተናጋሪው ማኅበረሰብ ብሔር አለመባላቸው ነው።

ለመሆኑ የኦሮሞዎች፣ የትግሬዎች፣ የዐማሮች፣ የአደሬዎች፣ የሱማሌዎች ብቻና ልዩ ባሕል፣ ምጣኔ ሃብት፣ የጋራ ግዛት የት ነበር ያለው? በኢትዮጵያ ውስጥ አንድም ነገድ በራሱ የጎሳ ድንበር ተወስኖ የኖረበት ዘመን በታሪክ በጭራሽ አይታወቅም። የኢትዮጵያ ሕዝብ በንግድ፣ በግብርና፣

በውትድርና፤ ከአንዱ ክፍል ወደሌላው በመሰደድ በሃብትና ሥልጣስን ሽሚያ ጦርነትና ወረራ ሳቢያ በማያቋርጥ ሁኔታ ሲደባለቁና ሲከፋፈሉ፣ እንደገና ሲዋሃዱ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና ባሕል ሲዳቀሉ የኖሩ በመሆናቸው አንዳቸውም በራሳቸው ድንበርና የጎሳ ክልል ተወስነው የኖሩበትና የሰፈሩበት <u>የብሔር ክልል</u> የለም። ታዲያ! የሌለውን ነገር እንዲኖር ታስቦ እነወያኔ ከፋሽስት ጣሊያን ወራሪዎች የተካኑትን የሥልጣን እድሚያቸውን በከፋፍለህ ግዛ ስልት ለማራዘም ሲሉ ብቻ የጎሣ ክልል በምዕራባውያን ድጋፍና ምክር አበጁ። ግን አይሳካም። ትርፉ ክስረት ነው። ኢትዮጵያ አገራችን በዓለም ላይ ለብዙ አያሌ ሺህ ዘመናት በልጆቹዋ መስዋእትነት ነፃነቷ አስከብራ የኖረች የጥቁር ሕዝብ ዘርያ ሁሉ የነፃነት ምሳሌና ጥንታዊ ሥልጣኔ አንጸባራቂ በመሆን ትታወቃለች። ይህን አኩሪ ታሪካችንና የነፃነት ምሳሌነት እንዳይኖር የሚፈልጉና እጅግ በጣም የሚያስቀናቸው ፀረ ኢትዮጵያ ኃይሎች ለብዙ ዘመናት ተደጋጋሚ ግልጽ ወረራና ጥፋት አድርገውብን እንኳ አልተሳካላቸውም ነበር። ዛሬ ደግሞ በሌላ አዲስ ስልት የጥፋት ተልዕኳቸው ቀጥሏል። በዚህም መሠረት በትውልድ አገር በቀል የሆኑትን በቅጥረኝነት አሰለፈዋል። በገንዘብ፣ በመረጃና በፖለቲካ መጠነ ሰፊ የተቀነባበረ ርዳታና ድጋፍ ቀረበላቸው። የጌቶቻቸውን ትእዛዝ ለማስፈፀም ሲባል በኢትዮጵያዊነት ላይ ስፊ ዘመቻ ነዙ ይነዛሉ። ለተልዕኳቸው መሳካት በቅድሚያ የፈጠራ የውሸት ታሪክ ይለፍፋሉ። የብሔር ብሔረሰብ የጎሣ ፖለቲክ ያራምዳሉ። የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ነገዶችን ርስ በርስ በማጋጨት ኢትዮጵያን ከዓለም ካርታ ላይ አስጠፍቶ ትንንሽ ቅጥረኛ አሽንጓሊቶችን በማስቀመጥ የአፍሪቃን ቀንድና የሕንድ ውቅያኖስ ጠረፍን፣ የአባይን ወንዝ ሸለቆና የቀይ ባሕር ቁልፍ የንግድ መሥመርን በቀጥታ ለመቆጣጠር የሚመኙ ኃይሎች አሉ።

## አርጎባ ብሎ ብሔረሰብ!

በጥንታዊው የአንኮበር ወረዳ ከበረከት ወሲል ጀምሮ አዋሽ ወንዝ በመለስ መተሐራና ፈንታሌ እስከ የይፋት ቆላማ ወረዳዎች አጋም ገበያ፣ ፋርሳ፣ አብዬ አገር፣ ወዘተረፈ የሚኖረውን ቆለኛ ገበሬ ቋንቋው ዐማርኛ ሃይማኖቱ በአብዛኛው እስልምና የሆነውን አንድ ሕዝብ በጅምላ "<u>የአርጎባ ብሔረሰብ</u>" ተብዬውን ምልክት በመለጠፍ አልፎ ተርፎም ከሦስት የባንቱስታን ክልል ውስጥ ማለትም በዐማራ፣ በኦሮሚያና አፋር ተሸነሸኑ። በአፈረ ክልል ውስጥ እንዲሆን

ለተደረገው እስላም ዐማራ የጋቸኔ፣ የፋርሳ፣ የዠገኔ አገር፣ የአክላስ አገር ወዘተረፈ ቀበሌዎች
ነዋሪውን ከዐማርኛ ሌላ ቋንቋ በጭራሽ የማይናገረውን ወገን በአፋር ክልል ተብዬው ውስጥ
"ልዩ ወረዳ" ተብሎ ተመድቧል።

ለኦሮሚያ በተከለሉት ቀበሌዎች ማለትም በአዋሽ፣ በፈንታሌ፣ በመተሐራ ወዘተረፈ የሚኖሩት
ከዐማርኛ ሌላ ኦሮምኛ የማያውቁት እስላሞች ሽማግሌዎችና ሕፃናት በአገራቸውና በምድራቸው
ሁለተኛ ዜጋ እንዲሆኑ ተወስኖባቸው በየወያኔ ተለጣፊ የኦሮሞ ጎሳ ታጣቂዎች ልዩ ይላማ
ሆነው የተገደሉትና የወያኔው የጎሣ ፖለቲካ ከነገሠበት ጀምሮ በየጊዜው የሚፈናቀሉትን
ቁጥር ቤቱ ይቁጠረው።

# በአርጎባ "ብሔረሰብ" ካባ የዋሃቢነት እስላም ሲስፋፋ

የወያኔው ፍጡር የአርጎባ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ተብዬው የፀረ ዐማራ ጥላቻ
ፕሮፖጋንዳ ዘመቻውን ተቀብሎ በሰፊው ያስተጋባል። ሁሉም እንደሚያውቀው ማንኛውም
የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር በዐማራው ላይ ብቻ እንደሚላከከው ባለፉት መንግሥታት የአርጎባን
መብት፣ ማንነት፣ ቋንቋ ወዘተረፈ ተጨቁኖ ነበር እየተባለ ይተረካል። አዲስ የፈጠራ ታሪክ
ይደጎሳል። ከሁሉም በላይ አክራሪ እስላሞችን ከውጪ በተለይም ከየመንና ሳውድ አረቢያ ወደ
አፋር ክልል እያስገቡ አርጎባውን በአዲስ መጤ አስተምህሮት እየሰበኩ ከፍተኛ ፀረ ዐማራ
ቅስቅሳ ያስደርጋሉ። የአርጎባ ወላስማ ካሊፋት፣ የይፋት ሡልጣናትን በአዲስ ለመመሥረት ፀረ
ክርስቲያን ጥላቻ በሳውዲ ጀማላዎች ገንዘብና ድጋፍ አበሻን በመላው ለማስለም አልመው
ይቅነዘነዛሉ። እስላሙን ዐማራ ገበሬ በክርስቲያን ወንድሙ ላይ ያነሳሱታል። ማኅበራዊ
ግንኙነቱን ሁሉ እንዲያቋርጥና በጠላትነት እንዲነሳ ይቀሰቅሱታል።

ልክ በፋሽስት ጣሊያን ወረራ ወቅት የጣሊያን መጢቃ ሰላቶ የእስላሞች የበላይ ጠባቂዎች
ሆነው በሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ የሱማሌና ሃማሴን አስካሪ ባንዳዎች ቀዳሚ ወራሪዎቻቸውን
እንዳዘመቱት ወያኔዎችም የስላም ወዳጅ መስለው በሕዝበ ክርስቲያኑ በያለበት ማዘመት
ጀምረዋል።

የወያኔው ተለጣፊ አርጎባ ከ1997 ዓ.ም ምርጭያ ወዲህ በሚገባ ተደራጅቶ ሰሜን ሸዋ ተብዬውን አካባቢ ሁሉንም ልዩ የአርጎባ ወረዳ ለማስደረግ በሰፊው ይንቀሳቀሳል። በቅርብ ጊዜ ውስጥ ምንጃርና ሸንኮራን፣ በረከትና ሶጠንን፣ መጠቅላያ፣ አሳግርትን መንዝና ይፋትን ሁሉን አጠቃሎ የአርጎባ ሡልጣናት ልዩ ወረዳ ለማስከለል ዝግጅቱ ተጠናቋል።

በዐማራ ክልል ተብየው ውስጥ የሚኖሩት ሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች መብታቸው ሲከበር በሌሎች ክልሎች ለምሳሌ በሐረር ከተማ፣ በድሬዳዋ በአርባጉጉ፣ በናዝሬት፣ በአዋሳ፣ በአሰላ፣ በግንደበረት፣ ወዘተረፈ የሚኖርው ብዙኃን ዐማርኛ ተናጋሪ ሕዝብ መብትየለሽ ነው። ልጆቹ በራሳቸው ቋንቋና ፊደል እንዲማሩ አይፈቀድም። የዜግነት መብት የላቸውም።

ዐማራው በሕዝቡ ብዛትና በሰፈረበት መልክአ ምድር ስፋት በማንኛውም ረገድ የወል ሕልናውን ለማስጠበቅ ብቃትና ችሎታ እያለው ሳለ ለምንድ ነው በአሁኑ ዘመን ለተፈለፈሉት የጎሳ መንጋ መፈንጭያ ሊሆን የቻለው?

ፕሮፌሰር ዓሥራት ነፍሳቸው ትማርና እንዳሉት የዐማራው ሕዝብ ችግር ዐማራው መሆኑን ነበር። በዚያን ጊዜ በዐማራው ሕዝብ ላይ በያለበት የደረሰውን ሰቆቃ ለመታደግ የተመሠረተውን መዐሕድ በጥብቅ ሲቃወም የነበረው የደላውና አውቅሁ ብሎ የሚንቦራቀቀው በሩቁ ሆኖ ፀጉር ሰንጣቂው፣ በምናቡ ጥቁር ወተት አላቢው፣ ነፋስ በወንፊት አጥማጁ ዐማራ ነበር። ሌላው ጥቂት ወገን ደግሞ ከጠላት ጋራ ተሞዳሙዶ፣ በጠቋሚነት፣ በአሳባቂነት፣ በአድርባይነት፣ በገዳይና አስገዳይነት፣ በገዛ ወንድሙ ላይ ከፍተኛ በደልና ግፍ ያደረሰውና እያደረሰም የሚገኘው ነው። በሌላው በኩልም እንዲሁ ትንሽ ክፍል ተኮላሽቶና ተኝቶ ያንቀላፉል። የተፈረንደሰው ቢቃጠልም እንኳ ሊሰማው ባለመቻሉ ከጨመደደው መጥፎ እንቅልፍ ና ድብርት ፈጽሞ አልነቃም ብሎ ሲድፈነፈን እግዜር ያደለው ጅብ ይጎርማምደዋል።

የምዕራቡ ተላላኪ ቅጥረኛ አሽከሮች በቅጥፈት፣ በጥላቻና በውሸት መልምለው ያሰማሯቸውን እነ ወያኔና ሻዕቢያን ለሥልጣን አበቅተው የኢትዮጵያ ልዑላዊነት ከተቀበረና የጎሣ ፖለቲካ ከሰኔ ወር 1983 ዓ.ም ጀምሮ ከነገሠ በኋላ በሁሉም መድረክ ላይ ዐማራውን መስደብ ማዋርድ፣ ሕዝብን በጎሣ ከፋፍሎ በማነሳሳት ዐማራዎችን ለጥቃት አደጋ ማጋለጥ፣ ዐማራውን ጨቋኝ፣ ነፍጠኛ፣ ትምክህተኛ ብሎ መፈረጅ፣ የወሎና የጎንደር ዐማራ ለም መሬቶችን ቆርሶ ለትግሬና

ለሱዳን መስጠት፣ ዐማራውን ባያለበት ትጥቅ አስፈትቶ ለጎሳ ታጣቂዎች ዳርጎ ማስጨፍጨፍ፣ ከትውልድ ቀዬው ማፈናቀል፣ በጎሣ ማፅዳት ዘመቻ ዐማራው በዐማራነቱ ተለይቶ ከየመንግሥት መሥሪያ ቤት በወረንጦ እየተለቀመ ከሥራው ማባረር፣ በኤርትራ ለተደረገው የገንጣይና አስገንጣይ ጦርነት ለጠፋው ሕይወትና ንብረት ተጠያቂው ዐማራው ብቻ እንደሆነ አስመስሉ ተወካዩችን በመላክ ይቅርታ በመጠየቅ ያማራውን ሕዝብ ክብር ማዋረድ፣ በደቡብና ምሥራቅ ኢትዮጵያ የሚኖሩት ዐማሮችን ለግዛት ማስፋፋት ወደሰው አገር የሄዱ ነፍጠኞች ናቸው እየተባለ ተለፍፏል ይለፈፋል። በዚህም ሳቢያ ስንት ሕይወትና ንብረት ወድሟል፤ ይወድማል፤ ትርኢቱም ተቀነባብሮ ይቀጥላል።

በመጀመሪያ ለጀርመን ድምፅ ራዲዮ ያቀረባችሁት አቶ ሰይድ ይመር ተብዬ የአካባቢው ተወላጅ አርጎባ በጭራሽ አይደለም። የወያኔ ተለጣፊ ሆዳም ዐማራ ተብዬዎች እንዳሉ ሁሉ አርጎባ ልሁን ወይም ልምሰል ባይ የወያኔ ትግሬዎችን የባንቱስታን አፓርታይድ ጎሳ ፖለቲ አቀንቃኝ ልዩ ምልምል ካድሬ ለመሆኑ ድርጊቱ ያስረዳል።

እንዴት ያልሞተ ቋንቋ ሞቶ ነበር፣ በአልዩ አምባ አርጎብኛ ይነገራል፣ ለአርጎብኛ መጻፊያ "የሳባ ፊደል" አወጣንለት ወዘተረፈ እያለ ቶሪናፋ ነዝቷል። ትልቁ ጉድ ደግሞ አርጎብኛ ያማርኛ ዘዬ ብቻ መሆኑ እየታወቀ ስለምን አዲስ ፊደል አስፈለገው? የኛን ፊደል የ"ሳባ" እያሉ የሚጠሩት ሁሉ ቅጠረኞችና ዘረኞች የነፃ አውጪ ጃርቶች ብቻ ናቸው። የኢትዮጵያ ግእዝ ፊደል በዐይነቱ ልዩ በእድሜም ከሳባ ተብዬው ይሁን ከሌሎቹ ፊደሎች ሁሉ የሚበልጥ ያባይ ሸለቆ ሥልጣኔ ቅርስ ነው።

አቶ ሰይድ ይመር ዐይኑን በጨው አጥቦ በአንኮበር ወረዳ በሓር አምባ ምክትል ወረዳ ጨፋ ሰፈር የሚኖሩት እስላም ዐማሮችን ከየመን የመጡ አረቦች ናቸው ብሎ ወሻክቷል። እረ! ያበሻ ዐማራ ሕዝብ ከዘላን አረመኔ ገና ከጎሳ የእድገት ደረጃ ከአላላፉት የመን አረብ ተብዬዎች ጋራ የዘር ሆነ የባሕል ዝምድና በጭራሽ የለውም። ያበሻ ሕዝብ ጥቁር አፍሪቃዊ እንጅ ያረብ አረመኔ ክልስ አይደለም። የሰው ዘር መገኛ ምንጭ አፍሪቃ ኢትዮጵያ እንጂ ያረብ ባሕረሰላጤ አይደለም። ከአረብ ድቅልቅል ዘር ወገን ነን የሚሉት ሱማሌዎች ሱዳኖች፣ የኤርትራ ዘላኖች ሁሉ የማንነት ቀውስ ያሳወራቸው እስላምናን ከዘር የማይለዩ ውዳቂዎች ናቸው።

የአረብ በደዊ ሁሉ የጥቁር አፍሪቃ ሕዝብን "አቢድ" ብሎ የሚጠላ መጥፎ ከአውሮፓ ነጭ ነኝ ባይ ዘረኛ እጅግ የባሰ መደዴ መሆናቸውን የሚያውቅ ያውቀዋል። በአበሳ ስደተኞችና የቤት ሠራተኞች ላይ እነዚህ አርመኔዎች የሚፈጽሙትን ኢሰባዊ ድርጊት ይገነዘቧል፡ ወራዳው መለሰ ዜናዊ ሙዐመር ጋዳፊ ገንዘብ ሲል ብቻ አረብ ነኝ፣ የመኒ ነኝ እያለ ሲዋሽ እንደነበረ ግን አይዘነጋም። ያርጎባን እስላም ሕዝብ የየመን አረብ ለማድረግ መቃጣትስ በግልጽ ፀረ ዐማራዎቹ እነወያኔና ሻዕቢያ ሲያቀነቁኑት የቆየ የተለመደ የውሸት ክምር ነው። ፀረ ኢትዮጵያውያን አገር በቀልና የባሕር ማዶ ኃይሎች ዘወትር የኢትዮጵያ ቀደምት አጤዎችን ማስጠላትና ማንቋሸሽ ዘመቻ ዘርፍ የሆነውን አቶ ስይድ ይመር እንበለ እፍረት አርጎባ የሚል መጠሪያ አወጡላቸው እያለ ዘላብዷል። አርጎባ እያሉ በግልጽ የሚጠሩትና አርጎባዎችንም የሚንቁና የሚጠሉትማ አደሬዎች ናቸው። አደሬዎች ራሳቸውን ከግብጽ ውጥቅንጥ አረቦች ጋራ እያዛመዱ ቆቱውንና አርጎባውን

እስላም ወንድማቸውን ሁሉ ባጣም አድርገው እንደሚንቁት እናውቃለን።

በሸዋ በባሕላዊ የተለምዶ አጠራር አርጎባዎች የእስላምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ዐማሮች ናቸው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ምእመናን ደግሞ ዐማራዎች ይባላሉ። የሸዋ እስላሞች ሁሉም እራስቸውን እስላም እንጂ "አርጎባ" ብለው እንደማይጠሩ መታወቅ አለበት።

በይፋትና አንኮበር በቆላው ምድር በሚገኙት ቀበሌዎች ለምሳሌ በዱለቻ፣ በጨኖ፣ በአብዩ አገር፤ በጋቸኔ፣ በአክላስ አገር፤ በሶጠን በፈንታሌ፣ በመተሐራና በመላው አዋሽ ሸለቆና አምባ የኖሩትና የሚኖሩት እስልምና የሚከተሉ ቋንቋቸው ግን ዐማርኛ የሆነ ሕዝብ እስከ ደርግ ዘመን 1967 ዓም ድረስ እስላሙና ክርስቲያኑ የሥጋ ዝምድና ያላቸው ባለርስት ነበሩ። የወላስማዎች፣ የመልከኞች ርስት ስሪት ጎን ለጎን ተፈጻሚ ሆኖ ለዘመናት የቆየውን የግል ይዞታ ሥርዓት አፍርሶ ሕዝቡ የመንግሥት ጭሰኛ ተደረገ።

የክርስቲያኖችና የእስላሞች መሪዎች ማለትም መርድ አዝማቾችና ወላስማዎች በታላቁ አጤ ኢያሱ አማካይነት ተባብረው ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ከግራኝ ወረራ መልስ በወረሞ ልዩልዩ ዘላን ሰፋሪዎች የተያዘባቸውን ሰፊ ምድር ለማስመለስ ያለሰለሰ ትግል ማደረጋቸው የተረጋገጠ ነው።

# ዜናሁ ዘአርጎባ?

በምሥራቅ ከዘይላ ጠረፍ በመለስ መላው ሐረርጌንና ጥንታዊውን ባሌን ይዞ በምዕራብ እስ እናሪያና ዐባይ ወንዝ ድረስ ሠፍረው የነበሩት ነባር ተወላጆች ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነበሩ። እነዚህም ሃድያዎች፣ ሃርላዎች፣ አላባ፣ ማርቆ፣ ጉራጌ፣ ዐማራ፣ ጋፋት ናቸው። ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ ሸለቆ ከቀድመ ታሪክ በፊት ጀምሮ ለመኖራቸው የዘመናዊው የቋንቋ ጥናትና የሥነ ጥንት ቅርስ ምርምር ያመለክታል። ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ አበሾች ከእሲያ ፈልሰው አልመጡም። ሴማውያን የሳባ ነገዶች ከአረቢያ ፈልሰው የአክሱምን ጥንታዊ ሥልጣኔ መሠረቱ አየተባለ የተነዛውና የሚነዛው የዘረኞች ትርኪ ምርኪ የፈጠራ ወሬ ነው። በተቃራኒው የአበሻ ሕዝብ ሥልጣኔ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ እንደተስፋፋ የእ ጃክሊን ፒረኑ፣ የሮጀር ሺናይደር፣ የዳቪድ አፕልዛርድ፣ የሩዶልፎ ፋቲሎቪች የአስረስ የኔ ሰው የአየለ በክሪ ወዘተረፈ ጥናት ያስረዳል።

እርግጥ ነው በዘመነ ክርስትና በኋላም የእስልምና ሃይማኖት በነቢዩ መሃመድ ከተጀመረና ከ7ኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ ሲስፋፋ የአረብ ነጋዲዎችና ስደተኞች በተለያዩ ጊዜያት ተሰደው የቀይ ባሕርን ተሻግረው በኢትዮጵያ ግዛት በዳህላቅ፣ በአደን ባሕረሰላጤ፣ በዘይላ፣ በርበራ፣ በሸ እንዲሁም በአፍሪቃ ቀንድና ምሥራቅ ጠርፎች በሞቃድሾ፣ በሞምባሳ፣ በማሊንዲ፣ በዛንዚባር ወዘተረፈ የሕንድ ውቅያኖስ የአፍሪቃ ጠረፎች በአጠቃላይ የየመን አረብ ነጋዴዎች ፈላሲዎች መስፈራቸው በትክክል ይታወቃል። ለምሳሌ በኢትዮጵያ ከ9ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በሸ ገብተው ከነባሩ የዐማራ ሕዝብ ጋራ ተጋብተው የነማዙሚና ሸዋ ሡልጣናት ከ9ነኛው ክፍ ዘመን እስከ 12ኛው ቀጥሎም የይፋት ሡልጣናት ሥርዎ መንግሥት ከ13ኛው እስከ 15ኛው ክ.ፍለ ዘመን መሥረተው እስከ ዘይላ በርበራ ድረስ ያለውን አገር ሲገዙ ለኢትዮጵያ አጤ መንግሥት እየገበሩ ለመኖረቸው ሰፊ የታሪክ ሰንድ ያረጋግጣል።

በሸዋ ምድር የእስልምናን ሃይማኖትን ያስገቡትና ያስፋፉት በተውፌት እንደሚነገረው የሸ ይፋት እስላሞች ሥር መሠረት አራተኛው ካሊፋ የነቢዩ አማች ማለትም የፋጢማ ባል የነበረውን ዓሊ ኢበን ጣሊብን (656- 661) የገደለው የአብዱረሃማን ውላጆች መሆናቸው በተውፌት ይነገራል። አብዱራሃማን በፈጸመው ወንጀል በሥቃላት የሞት ፍርድ ሲቀጣ

ዘርያዎቹ በአረብ አገር ለመኖር ስላልቻሉ ወደ አበሻ አገር ተሰደው በኤደን ባሕረ ሰላጤ በኩል ወደ መሓል አገር ሸዋ ገብተው ተደበቁ። ከነባሩ የዐማራ ሕዝብ ጋራ ተጋብተው የእስልምና ሃይማኖታቸውን አስፋፉ። በዚህም ሂደት በኢትዮጵያ ውስጥ የሸዋ ሱልጣናት ያካባቢ መንግሥትን መሠረቱ። የይፋት ወላስማዎች መጠሪያ ስማቸውን ያገኙት ከዐማርኛው ቃል "ይፋ" ነው። ባማርኛ ይፋት፣ በግእዝ ዊፋት፣ ባረብኛ ወፈት ይባላል። ይፋ ማላት ግልጥ፣ ስውር ድብቅ ያልሆነ ነገርን ይገልፃል። በክርስቲያኑ አጤ አገርና ምድር ደቡብ ምሥራቅ ላይ በሩቅ ተደብቀውና ተሸሽገው የኖሩት ቀስ በቀስ እስልምናን በይፋ መስበክና ማስረጨት የጀመሩት የአብዱራሃማን ውላጆች አርጎባ ተብለዋል።

የአርጎባ ትርጉምም አረብ ገባ ማለት ነው። የማስለሙ ሂደት ስለተስፋፋና ይፋ ስለሆነ ቀደም ብሎ እንደተገለጸው አገሩ ይፋት ሕዝቡም አርጎባ ገዥው ወይም አበጋዙ ደግሞ ወላስማ በመባል ይታወቃል። የአርጎባ ወገን ደባ፣ ሻጉራና ቃጭኖ ይባላሉ።

ነገር ግን ዛሬ በይፋትና አንኮበር የሚኖሩት "አርጎባዎች" ራሳቸውን አርጎባ ሳይሆን እስላም ብለው ነው የሚጠሩት። እስላም የሆኑ የሐረርጌ ቆቱዎችና አሩሲዎች ሁሉ እራሳቸውን እስላማ እንጂ ኦሮሞ ብለው እንደማይጠሩት ነው።

የሸዋ ሱልጣናት እስከ 13ኛው ክ.ዘመን ድረስ ቆይት በይፋት ተቀናቃኙ ተሸነፈ። የይፋት ሱልጣናት በኃይል ተደራጅቶ ለኢትዮጵያ አጤ ንጉሠ ነገሥት አልገብርም በማለት ተከታታይ ጦርነት አድርጎ በአጤ ዘርአ ያዕቆብ ዘመን (1434 እስከ 1468 ዓ.ም) ስለተሸነፉ ዋና ማዕከሉን ከይፋት ወደ አዳል በርሃ ቀጥሎም ወደ ሐረርጌ አዛወረ። የሐረር ከተማንም ቆረቆረ። በሐረር ጀጉል ውስጥ የሚኖሩት አደሬዎችና ባካባቢው ሰፍረው የሚኖሩት አርጎባዎች በቀጥታ ከሸዋ ይፋት ሱልጣናት የወረዱ ናቸው።

የጥንት ሸዋ እስላሞች ከባሪያ ፈንጋይና ነጋዴ ጀበርቲ እስላሞች ጋራ ምንም ዓይነት የዘር ግንኙነት የላቸውም። በመላው አፍሪቃ የባሪያ ንግድ ተደርጓል። በሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ ከግብፅ እስከ ሞዛምቢክ ድረስ ባሉት ጠረፎች እንደ ምጽዋ፣ ታጁራ፣ ዘይላ፣ ብርበራ፣ ሞቃዲሾ፣ ማሊንዲ፣ ሞምባሳ፣ ዛንዚባር፣ ደረሰላም፣ ፒምባ፣ ወዘተረፈ ለቱርክና አረብ ገበያ

ባሪያ ማቅረቢያ ጣቢያዎች ነበሩ። ነጋዴዎቹም አረቦችና የአካባቢው ተወላጅ እስላሞች እንደነበሩ ይታወቃል። በተለይም ጀበርቲና ወርጂ የተባሉት እሳላም ነጋዴዎች በመላው ሰሜንና ምሥራቅ አፍሪቃ ነግደዋል።

ጀበርቲዎች ያረብ ክልሶች ሲሆኑ በሐረርጌ፣ በታጁራ፣ ዘይላና በርበራ ሠፍረው ነበር።

በአፍሪቃ ቀንድ የጀበርቴዎች ታሪክ ከ11ኛው ክ.ዘመን ሼህ ኢስማኤል ጀበርቲ የዳሮድ ሱማሌ ጎሣ ቅድማያት ከአረቢያ ፈልሶ ሰሜን ምሥራቅ ሱማሌ ገብቶ ሠፈረ።

የጀበርቴ ባሪያ ነጋዴዎች ገበያውን በሞኖፖል ይዘው ያለምንም ችግር ለግብፅና አረቢ እንዲሁም ለፋርስ  የባሪያ ገብያ አቅራቢዎች ነበሩ። ንግዱ በአብዛኛው ወጣቶችን በተለይም ልጃገረዶችን ይመለከታል። ወጣቶቹ የሚመጡበት አካባቢ ደቡብና ምዕራብ ደቡብ ኢትዮጵያ ሲሆን የጋላና ሲዳማ አባቆሮዎች ደካማ ከሆኑት ጎረቤቶቻቸውና በመካከላቸው ባለው ጦርነት ባሪያ ፍንገለና ማደን እንደነበረና ብቀይና ጥቁር ባሮች መካከል ልዩነት መኖሩን የፒ ኢ ለቭጆይ ጥናት ያስረዳል።

"The slave trade was largely a trade in children especially girls. The children were brought from regions south and Southwestern Ethiopia. Thae Galla and Sidama principalities obtained many of these children in slave raids on their waker  neighbours or in disputes between themselves.... A distinction was made beween the "red" and "black" slaves."   (P.E.Lovejoy: *Transformation in Slavery*, (Cambridge: 1983),PP.149-150)

# ምድረ አርጎባ

የአርጎባዎች ጥንት አገርና ምድር ፈጠጋር (አሩሲ)፣ ይፋት፣ ላይ ደዋሮ፣ ታች ደዋሮ፣ ባሌ፣ ሃድያ፣ ወጂ፣ ዳሞት፤ ሃርላ፣ ገንዝ ናቸው።

ይህም ማለት ዛሬ አሩሲ ነገሌ፣ አርባጉጉ አውራጃ፣ ሃብሩ፣ የረርና ከረዩ አውራጃ፤ ወበራ ሐረር ዙሩያ፣ ጋራ ሙለታ፣ ጉርሱም፣ ጨርጨርና ጋራጉራቻ ናቸው።

ኢትዮጵያ በልጆቿ መስዋዕትነት ለዘለዓለም ትኖራለች!

አዩ ሞሚና ይስማን
ፕሮፌሰር፣ ሥነ አፍሪቃ
ሥነ ግብፅ
ሥነ ቋንቋና ታሪክ